**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**በኦሮሚያ ክልል በሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች ላይ ሲካሄድ የቆየው ህዝባዊ ምክክር እና ግብአት የማሰባሰብ መርሀ-ግብር መጠናቀቅን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ**

የኢትዮጵያ መንግስት - የሽግግር ፍትህ ስርአትን ተግባራዊ ማድረግ - ለአገራችን ዘላቂ ሠላም፣ ዲሞክራሲ እና ፍትህ የሰፈነበት ስርአት ግንባታ ጉልህ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመገንዘብ - ሂደቱን በተሟላና በተቀናጀ መልኩ ለመተግበር የሚያስችሉ የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

በዚህ ረገድ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የማርቀቅ ስራ ለመጀመር የሚያስችለው 'የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች' መነሻ ሰነድ የፍትህ ሚኒስቴር ባደራጀው ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን የተዘጋጀ ሲሆን - ለፖሊሲ ዝግጅት እና ግብአት አሰባሰብ የሚያስፈልገው ብሄራዊ ምክክር የማስጀመሪያ ስነ-ስርአት የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተከናውኗል።

ይህን ተከትሎም በክልሎች ደረጃ የሚካሄደው ህዝባዊ ምክክር በመላው አገሪቱ በሚገኙ ከሀምሳ ስምንት በላይ ከተሞች ከሚያዝያ እስከ ነሐሴ 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለማከናወን መርሀ-ግብር ወጥቷል። በዚህ አግባብ የመጀመሪያው ምእራፍ የህዝብ ምክክር በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ 12 ከተሞች (አዳማ፣ አሰላ፣ ጪሮ፣ ሻሸመኔ፣ ባሌ ሮቤ፣ ቡሌ ሆራ፣ ኣዶላ፣ ወሊሶ፣ አምቦ፣ ጅማ፣ መቱ እና ነቀምት) ከሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በስኬት እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተካሂዷል።

በሁሉም የምክክር መድረኮች ላይ ፍጹም ገለልተኛ እና የሂደቱን ልዩ ግብ ታሳቢ ባደረገ ሂደት የተመረጡ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂ ግለሰቦች፣ የእምነት እና የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ የወጣቶች እኛ ሴቶች ተወካዮች፣ እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ድምጽ የሚወክሉ ባለድርሻ አካላት በከፍተኛ ንቃት ተሳትፈዋል። በባለሙያዎች በቀረቡ አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች ላይ ሰፊ ክርክር አካሂደዋል። ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስኟቸውን የማጠናከሪያ እና በአማራጭነት ሊያዙ የሚገቡ ምክረ-ሀሳቦችንም በስፋት አቅርበዋል።

በጥቅሉ ሲታይ - ከየከተሞቹ እና ራቅ ካሉ አዋሳኝ ወረዳዎች የተጋበዘው ህዝብ በሙሉ - ረጅም ጉዞ በመጓዝ፣ በየመድረኮቹ ያለምንም መጓደል በመገኘት፣ እና በምክክር መድረኮቹ ላይም ከታቀደው በላይ ረጃጅም ሰአታትን በመጠቀም ያሳየው በባለቤትነት ስሜት የታጀበ ከፍተኛ ተሳትፎ - ገና ከጅምሩ ህዝቡ በሂደቱ ላይ ያለውን ጠንካራ እምነት ያሳየበት አጋጣሚ ሆኖ አልፏል። ለዚህም ከፍተኛ ክብር እና ምስጋና ይገባዋል።

በዚህ አጋጣሚ ከሰነዶች ዝግጅት ጀምሮ - በቦታዎች እና ተሳታፊዎች መረጣ እና በሎጂስቲክስ እና ፋይናንስ ዝግጅት ባሉ የምክክር ሂደቶቹ ስራዎች አይነተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

**የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን**<br>
**ፍትህ ሚኒስቴር**<br>
**ግንቦት 24 ቀን 2015 ዓ.ም**